# የአገርና ህዝብ ሉዓላዊነት የተዋረዱና የተደፈሩባት ኢትዮጵያ

ከበላይ መታፈሪያ ዶ/ር

የአማራ ህዝብና ኢትዮጵያዊነት ማንነት፥ ተደፍሮና ተንቀው ሉዓላዊ የአገር ዳር ዲንበራችን ተጥሷል

1ኛ/ ከላይ በሱዳን መንግስት ከ50_ 60 ኪሎሜትር ወደውስጥና በቁመት ደግሞ እስከ 170 ኪሎሜትር ዘልቆ በመግባት የአማራ እርስትን ለም መሬት ወርሮ እያረሰና የአገርን ሀብትና ንብረት እየዘረፈ ከመሆን ጋር ነጋ መሽ የአማራ ህዝብ እየተገደለና ንብረቱ እየተጫነ፥ ከብቱ እየተነዳ ሦሥት አመት አለፈው። ይህ እንዴትና ለምን ሆነ? ለማስለቀቅ ለምን አልተሞከረም፥ ለምን ዝምተባለ?አብይ አህመድ ፈቅዶልን ነው ወረራውን የፈጸምነው ብለዋል ። የኮሎኔል አብይ ይሀን ለምንና እንዴት በአገር ሉዓላዊነት ላይ ማዘዝና ማስፈጸም ቻለ? ለህዝባችን በተለይም ለጎንደር አማራ መልስና ግልጽነት ያለው መንግስት ነኝ ተብየው አስቸኳይ መልስ መስጠትና መሬታችንን ማስመለስ የህዝብና የአገር ሉዓላዊነት መከበር አለበት። የአማራ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው። የአገር ሉዓላዊነት ከብናኝ አፈረ ይጀምራል፤ለዚህም ነው የእኛ ቀደምት አገር አስከባሪ ትውልዶች በእግር ጫማ ላይ ያለ አፈር እንዳይወጣ ይጠብቁ ነበር።

2ኛ/ደቡብ ሱዳን እንደዚሁ የኢትዮጵያን ዳር ዲንበር በተደጋጋሚ ከ200 ኪሎሜትር በላይ በዘለቀ በጋንቤላ በኩል ጥሶ በመግባት ልጆችን ፣ ሀብት ንብረት ከብትን ጨምሮ በመዝረፍና ህዝብን በማስቃየት ላይ ሲሆኑ ግን መንግስት ተብየው ህዝባችን ለሚጠይቀው መልስ ከመስጠት እየዋሸና እያለባበስ የሚመልሰው፣ ህዝብን ማታለል እንጂ ለአገር ሉዓላዊነትን፣ የህዝብን ማንነትና ክብርን ያላበሰ አይደለም። በመሆኑም ኢትዮጵያ ተደፍራለች ተዋርዳለች። ይህ ጉዳይ ለምን አልተከበረም? ለምንና በምን ዓይነት አመክኒው ነው አገር እየተመራች ያለችው?
አገር በባንዳና በተገንጣይ ኦሮሙማ ጽንፈኞች/አነግ መሪ አብይ አህመድ እየተመራች ሰላም፣ ክብርና ደህንነትን አታገኝም። ጽንፈኞችን፣ ውሸታምንና ሆዳሞችን ማሰወገድ የግድ ይላታል።

3ኛ/ ከወንጀለኛው ወያኔ ህውሃት ጋር ፕሪቶሪያ ላይ የተካሄደው ስምምነት አማራን ያገለለና ከኢትዮጵያ ህዝብ ስውር በሆነና ቅቡልነትን ያጣ እምነትን ያግደለ ከመሆን ጋር ለአገር ጉዳት፣ ለግለሰቦች ደህንነት እና ወያኔ ህውሃትን በሚጠቅም መልኩ የተፈጸመ የሴራ ቅንብርና የኢትዮጵያ ጠላቶች ተግባር ነበር። ስለዚህ በኢትዮጵያኖች ዘንድ ተቀባይነት የሌለውና ስምምነቱ ለመላ ህዝባችን ግልፅነት የለውም ውድቅም ነው። ህዝባችን ቅቡልነት ያለው መልስን ደጋግሞና አበክሮ ይጠይቃል።

4ኛ/ ህውሃት ወያኔ በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት መሰረት እንደተወራው ለምንና እንዴት ትጥቅ እንዲፈታ አልሆነ? ለምንና ለምንስ ጉዳይ ይተግባራዊ ሲሆን አይታየም ?ይህ ለህዝብ ግልፅ መሆን አለበት?

5ኛ/የወልቃይትና የራያ ህዝብ አማራ ነው፣ መሬቱም እርስቱ ነው።ይህ ማንነቱ እንዲታዎቅና እንዲከበርለት የሚጠይቀው ጥያቄ እንዲከበርለት ጠይቋል ፣መልስንም ያለ ወለም ዘለም ይፈልጋል። ለምንና ለምንስ ጉዳይ ግልፅነት በእውነት፣ በቅን አይመለስም?

6ኛ/ ወያኔ/ ህውሃት ወንጀለኛና ከሃዲ፡ ሌባና ዘራፊ አጋሚዶ፣ መከላከያ ላይ ክህደት የፈጸመና የገደለ፣ የአገርም ክህደትን የፈጸመ ይቅር የማይባል የህግ ተጠያቂነት ያለው በፓርላማም ሽብርተኛ ተብሎ የተፈረደበት ሆኖ እያለ ያለበቂና ግልፅነት በጎደለው አመክኒዎ ስለም ከሽብርተኝነት ተነሳለት ?የህዝባች የጠበቀና ከፍተኛ ጥያቄ ሲሆን፣መልስን ከመንግስት ይፈልጋል?

7ኛ/ የህዝብ ደህንነትና ሰላም መንግስት ከሚባለው አካል የመጀመሪያና ተቀዳሚው ተግባሩ ነው። የአብይ የኦሮሙማው መንግስት ተብየው ግን አማራን አክርሮ በከፋ ጠላቻ ላይ ተጠምዶ ሸኔ የሚባል ነብሰገዳይ በማደራጀት በማስታጠቅና ባንኮችን በማዘረፍ በወለጋ ውስጥ አማራን በማስጨፍጨፍ የደም ጎርፍ እደወንዝ ሙላት ለ5 ዓመት ያለማቋረጥ እየፈስሰ ነው።ለምን ጉዳይ ነው ይህ እብሪትና አረመኔዊ ተግባር በንፀሃን አማራ ህዝብ ላይ የሚፈጸመና ሃግ ያይባለትስ ምክንያት ለምን ነው ? ሸኔ ገዳይ ወንጀለኛ ከሁሉ በፊት መፍረስና መጥፋት ያለበት ሆኖ ሳለ ለምን አልተሞከረም ?

8ኛኛ/ ልዩ ኃይሎች ይፍረሱ ከተባለ የክልል ኃይሎች በቅድሚያ መፍረስ ያለባቸውና መጀመር ያለበት ከኦሮሞ ክልል፣ ከሸኔና ኦነግና ከክልሉ ልዩ ኃይል ነው። በመቀጠልም ከትግራይ ክልልና እንደ አስፈላጊነቱ ተዋረድ መፈጸምን ይጠይቃል። ሌላው ልዩ ሁሉ ከፈረስ በኃላ የአማራ ህዝብ ደህንነት የተጠበቀ ሆኖ ሲገኝና ህዝቡ ከውጭ ጠላትና ከውስጥ ቦርቧሪ ባንዳ ነፃ መሆኑን የአማራ ህዝብ ሲያረጋግጠው ያን ጊዜ የአማራ ክልል ልዩ ኃይል ያስረክባል፡ አሁን ግን አይታሰብም ፣ አይሆንም።

9ኛ/ የአማራ ልዩ ኃይል ግን በሁሉም አቅጣጫ በጠላት የተከበበና የግዛት ክልሉም በውጭ ወራሪ የተያዘበት፣ በወልቃይትና ራያ በወያኔ ባንዳው ከበበና በጦርነት ውስጥ ለሆነ፣ የአገር ዳር ዲንበሩን መከበር ከአረጋገጠና መከላከያው ኢትዮጵያዊነት ያለውንና የአገር ሉዓላዊነትን ለመጠበቅ ብቃት ያለው ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው።

10ኛ/አሁን በአማራ ክልል የተጀመረው አመፅ ተቀጣጥሎ መፋፋመና ህዝቧችንን ለድል የሚያበቃ መሆን አለበት።ይህ የህዝብ አመፅ ግፍ፣ መከራ፣ስቃይ፣ህዝብሞት ፣ደም እንደ ወንዝ ውሃ የፈሰሰበ ፣ የተፈናቀለና ዘሩ ፣ቋንቋው ተለይቶ የተገደለበት፣ አማራ በታሪካችን የተናቀበትና ውርደት የተቀበለበት ዘመን ነው። ስለሆነም ይህ የተጀመረ የከፋው ህዝብ አመፅ እንደ ወያኔ በአፈ ጮሌዎች መታለልና መሰለብ የለበትም። ትግሉ በብልሃት በብልጠትና ጥበብን በተላበሰ የሚመራ ሆኖ የማይበርድና ብዙ ክልሎችን ያቀፈና ያካተተ የዘር፣ የቋንቋ ፖለቲካን ለአንደየና ለመጨረሻ መስበር፣ መደምሰስና በማጥፋት አገርን የሚያድን ህዝብ ለነፃ የሚያበቃ መሆን አለበት። ለዚህ ለተቀጣጠለው ህዝባዊ አመፅ ፣ብርቱ፣የማይበገር፣ የማይገስስ ፅኑ የኢትዮጵያን አለኝታ፣ የትውልድ ብሩህ ተስፋን የሚያረጋግጥ የህዝብ ድል እንድሆን መመራት እጅግ ታለቅነት ነው።የዚህ ትግል ዓላማ፣ግቡና መዳረሻ ይህን የብሄር የዘር ፣ የባንዳና ጽንፈኛ ተገንጣይ ተረኛ ኦሮሞ መንግስትን ከኢትዮጵያ ማስውገድና መቅበር ነው። በምትኩም ኢትዮጵያዊ መንግስትን እውን ማድረግና ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነትና አረንጓዴ_ቢጫ_ቀይ ሰንደቅዓላማን ማረጋገጥ ነው።

11ኛ/ የብሔር ብሔረሰብ ከፋፋይ ህገ_ወጥ ህገ_መንግስት ተቀይሮና የክልል መንግስት ፈርሶ፣ አዲስ በህዝብ ተካፍሎና አመኔታ የደቀ ሲጻፍ፣ ህዝባዊ ህገ መንግስት በኢትዮጵያዊነት ሲጸድቅ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነት እናረጋግጣሉ።

12ኛ/ በህዝበ ውሳኔ ህዝብ የመረጠው፣ ህዝብ ያመነውና አመኔታ ያሳደረበት አገርና ህዝብን ይመራል እንጂ ከአሁን በኃላ በአምባገነን እብሪተኛና በባንዳ አረመኔ ኢትዮጵያ አትመራም።የተጀመረትግ ተፋፉሞ የኢትዮጵን ትንሣኤ ያበስራል።
**ምንጊዜም ኢትዮጵያ !!!** **ህዝብ ያሸንፋል!!!**